# ደንብ

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**የተዛመዱ ርእሶች፡-** JEA-RA፣ JEB-RA፣ JEE፣ JEE-RA
**ሃላፊ ፅ/ቤት፡-** ዋና የአካዴሚ መኮንን
የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ

## ከክፍልና ከት/ቤት የተማሪ መወገዶች

### I. ኣላማ

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ከነጠላ መማርያ ክፍሎች መወገዶች እና ከMontgomery County Public Schools (MCPS) ዘላቂ መወገድ ቅደም ተከተሎች ለማስቀመጥ

### II. ፍቺ

ኣንድ *ብቁ ተማሪ* እድሜው/ዋ ኣስራስምንት (18) ኣመቶች ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ወይም ነፃ የወጣ/ች ኣንድ ተማሪ ነው/ናት።

### III. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. ከነጠላ መማርያ ክፍሎች መወገድ

1. በት/ቤት-የተቀሰቀሰ የተማሪ ከክፍል መወገድ መነሻው ተማሪው/ዋ (1) ኣዘውትሮ/ራ ወይም በሃይል የት/ቤትን እንቅስቃሴዎች ከረበሸ/ች ወይም (2) ተማሪው/ዋ በሚገባ ባልተዘጋጀ(ች)በት ኮርስ ውስጥ የተመደበ(ች)በት መረጃ ሲቀርብ። የት/ቤት ሰራተኛ ኣባሎች ከተማሪው/ዋ፣ ወላጆቹ(ቿ)/ኣሳዳጊዎቹ(ቿ)፣ እና ከከተሳታፊ መምህራን ጋር ተሰብስቦ የመወገድ ሃሳብ ከማቅረባቸው በፊት፣ ተገቢ ከሆነም፣ በትብብሮሽ ፕሮብሌም-መፍቻ ስብሰባ(ዎች) በማካሄድ ተማሪው/ዋ የኮርስ ተፈላጊዎችን ለማሟላት ለማገዝ የተቻላቸውን ያህል ጥረት ማድረግ ኣለባቸው። ኣስተዳዳሪው/ተወካዩ ባለው መረጃ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል። ስብሰባው በMCPS ፎርም 272-10፣ *የግል-ቃንብኑቶች ሰነዳ* በመግለገል መሰነድ ኣለበት።

2. በተማሪ-የተቀሰቀሰ መወገድ የሚከናወነው ተማሪው/ዋ እና ወላጆች/ኣሳዳጊዎች መወገድ ለተማሪው/ዋ ጠቃሚ ነው ብለው ሲወስኑ ነው። የብቁ ተማሪ መወገድ በኣማካሪ ድህረ እይታ እንዲደረግበት የሚያስፈልግ ሲሆን ከወላጆች/ኣሳዳጊዎችም ጋር ውይይት ሊደረግበት ይችላል። ተማሪው/ዋ ብቁ ተማሪ ካልሆነ/ች፣ ተማሪው/ዋ ከኣንድ ኮርስ ከተወገደ/ች የምረቃ ተፈላጊዎችን ለማሟላት የመዘግየት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ግንዛቤ መኖሩን ለማረጋገጥ የተማሪው/ዋ የመወገድ ጥያቄ በወላጆች/ኣሳዳጊዎች በፅሁፍ መጽደቅ፣ በኣማካሪ መገምገም፣ እናም ከተማሪው/ዋ ጋር ውይይት መካሄድ ኣለበት። የኣማካሪ የውሳኔ ሃሳብ እንዲፀድቅ ወይም ውድቅ እንዲደረግ ለኣስተዳዳሪ/ተወካይ መተላለፍ ኣለበት።

3. እንደ ተገቢነቱ፣ ለተማሪው/ዋ ከመማርያ ክፍል መወገድ አማራጮች እንዲኖሩ(ሯ)ት ያስፈልጋል። ተማሪዉ/ዋ በቂ የትምህርት ዝግጅት ባለዉ/ላት በተመሳሳይ የርእስ መስክ ወደ ሌላ ኮርስ ሊ(ልት)ዛወር ይችላል/ትችላለች። እንደዚህ ዓይነቱ አማራጭ ከሌለ ተማሪው/ዋ ወደ ተገቢው በምርጫ ወደሚወሰድ /elective ኮርስ ሊ(ልት)ዛወር ይችላል/ትችላለች። ከተፈለገና እንደ አግባቡ አስተዳዳሪዎች/ወኪሎቻቸው የተማሪ ፕሮግራ የማስተካከል ፈቃድም ሊኖራቸው ይችላል።

4. ማርኮችና ክሬዲቶች በሚከተሉት መመርያዎች መሰረት ይሰጣሉ፡-

   a) አንድ/ዲት ተማሪ ከአምስተኛው ሳምንት (25 የትምህርት ቀኖች) መጨረሻ በፊት ከኮርስ ከተወገደ/ች፣ በተማሪው/ዋ ቋሚ መዝገብ ወይም ሪፖርት ካርድ ላይ ምንም ማስታወሻ አይደረግም።

   b) አንድ/ዲት ተማሪ ከአምስተኛው ሳምንት (25 የትምህርት ቀኖች) መጨረሻ በኋላ ከኮርስ ከተወገደ/ች፣ "withdrew/ተወገደ" ወይም "W"፣ የመወገጃ ቀን፣ እና ማርኩ እስከ የመወገጃ ቀን አማካዩ ተሰልቶ ሪፖርት ካርዱ እና ቋሚ መዝገቡ ላይ ይመዘገባል።

   c) ተማሪው/ዋ በተመሳሳይ ርእስ መስክ ውስጥ ወደሚገኝ ኮርስ ከተዛወረ/ች፣ በስኬታማ ለተፈፀሙ ለእነዚያ ኮርሶች ክሬዲት ይሰጣል።

B. በቋሚነት/በዘላቂነት ከት/ቤት መወገድ

1. አንድ የሰራተኛ አባል፣ ቢያንስ 18 ኣመት እድሜ ያለው/ያላት፣ ተማሪ በዘላቂ ከት/ቤት መወገዱ(ዷ)ን ካወቀ/ች፣ ያ(ቿ)ው ሰራተኛ ለት/ቤቱ አስተዳዳሪ ማስታወቅ አለበ(ባ)ት፣ ይህም አስተዳዳሪ ተማሪው/ዋ በወቅታዊው፣ ወይም በሌላ ተስማሚ፣ የMCPS ፕሮግራም እንደሚከተለው እንዲ(ድት)ቆይ ማበረታታት አለበት፡-

   a) የMCPS ፎርም 565-4a፣ *መወገድን ለመከላከል ትምህርታዊ ቃለመጠይቅን* በመሙላት የትምህርታዊ ቃለመጠይቅ ማከናወን።

   b) ከተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ጠበቃዎች፣ መምህራን፣ አማካሪዎች፣ እና የአስተዳደር ሰራተኞች ጋር፣ እንደ አግባቡ፣ የፕሮብሌም-አፈታት ስብሰባ ማካሄድ። ወላጆች/አሳዳጊዎችን በተቻለ ፍጥነት ማሳወቅና በሂደቱ ማሳተፍ አስገዳጅ ነው። የቋንቋ አስተርጓሚዎች እንዳስፈላጊነቱ መገኘት አለባቸው።

2. እላይ ያሉት እርምጃዎች ከተሟሉ በኋላ፣ ተማሪው/ዋ በዘላቂ መወገድ ለመግፋት አዝማሚያ ከቀፀለ/ች፣ የት/ቤት ሰራተኞች የMCPS ፎርም 565-4፣ *ከት/ቤት በዘላቂ መወገደን* መሙላት አለባቸው። የMCPS ፎርም 565-4፣ *ከት/ቤት በዘላቂ መወገድ*፣ እና 565-4a፣ *ትምህርታዊ ቃለመጠይቅ በዘላቂነት መወገድ* ቅጂዎች በፎርሞቹ በተመለከተው መሰረት መሰራጨት አለባቸው።

**የተዛመዱ ምንጮች፡-** የሜሪላንድ አኖቴትድ ኮድ፣ *የትምህርት አንቀፅ*፣ §7-301፣ እና *አጠቃላይ ደንቦች/Provisions*፣ §1-401፤ *የሜሪላንድ ደንቦች ኮድ* 13A.08.01.01 እና 13A.08.01.07e

***የደንብ ታሪክ፦*** ተቀዳሚ ደንብ 515-2፣ ጃንዩወሪ 4፣ 1979፣ ዲሰምበር 1986 የተከለሰ፣ ሴፕቴምበር 24፣ 2012 የተከለሰ፣ ሜይ 15፣ 2015 የተከለሰ፣ ጁን 19፣ 2017 የተከለሰ።